# <u>በልሳን መናገር ማለት ምን ማለት ነው?</u>

አንዳንድ ሰዎች ስለ ልሳን ያላቸው ግንዛቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ ጋር ስናስተያየው ትክከል አለመሆናቸውን እገነዘባለው። ስለዚህ በዚህ ጽሁፌ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ልሳን ትክክለኛ ትርጓሜ እንመለከታለን። መልካም ንባብ

በሐዋሪያት ስራ ላይ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል አስቀድሞ ቃል ገብቶላቸው ነበር። በበዓለ 50 ላይ (ጴንጤቆስጤ ላይ) ብዙ ሰዎች ይህንን በዓል ለማክበር ከተለያዩ ቦታዎች (ከ14 ቦታዎች በላይ) ይመጡ ነበር። ሐዋ 2፡5 እና ቁጥር 9-12። እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት የየራሳቸው ቋንቋ አላቸው። ደቀመዛሙርቱ ግን አይሁዶች ስለነበሩ የሌሎችን ቋንቋ መናገር አይችሉም ነበር። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። ደቀመዛሙርቱም እያንዳንዱ ሰው በገዛ ቋንቋው ሲናገር ይሰሙት ነበር። ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነጥብ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ልሳን ማለት በቀላሉ ቋንቋ ማለት ነው። ቋንቋ ማለት ደግሞ ትርጉም ያለው ነገር ነው። እዚህ ጋ ነው እንግዲህ ብዙ ሰው የሚስተው። ወደ ሐዋሪያት መጽሐፍ ልመልሳችሁና አንዳንድ ነጥብ አብረን እንመልከት።

1. ይህ ቋንቋ የመላዕክት ቋንቋ ወይም እግዚአብሔርና ተናጋሪው ብቻ የሚያውቅ ቋንቋ አይደለም። በዚሁ መጽሐፍ ላይ ሰዎች ተሰብስበው ልሳን ሲናገሩ የሌሎች ሰዎች መልስ ተመልከቱ፤ ሐዋ 2፡6-8 "ይህን ድምጽ ሲሰሙ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤ #እያንዳንዱም_ሰው፣ #ሰዎቹ_በገዛ_ቋንቋው ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ በመገረምና በመደነቅም እንዲህ አሉ "እነዚህ የሚናገሩት #የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ፣ #እያንዳንዳችን_በተወለድንበት፣ #በራሳችን_ቋንቋ ሲናገሩ #የምንሰማቸው እንዴት ቢሆን ነው?" " ይህ ክፍል በግልጽ ቋንቋው የመላዕክት ወይም አንዳንዶች እንደሚናገሩት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ብቻ የሚነገር ቋንቋ አለመሆኑን ነው።
2. እግዚአብሔር ይህንን የፈቀደበት ምክንያት ይህንን በዓል ለማክበር ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ሰዎች ወንጌልን መስማት ነበረባቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንዳይተላለፍ የሚያደርግ አንድ ነገር ተከሰተ። እሱም የቋንቋ ችግር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ልኮ ሰዎቹ በራሳቸው ቋንቋ እንዲሰሙ አደረገ። ይህ ደግሞ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ታላቁ ተልዕኮ ነበር። ማቴ 28፡19-20

ይህ ጽሁፍ በጣም በአጭር የጻፍኩት ሰዎች ረጅም ጽሐፍ በማንበብ እንዳይሰላቹ በማለት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ብቻ እንስማ። ሰማይ የማያቀውን፣ ሰዎች የማያቁት ቋንቋ እግዚአብሔር እንዲህ ተናገረኝ የሚለው አባባል በምንም መስፈርት የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አይደለም። በሚቀጥለው ደግሞ "የጴንጤቆስጤ እውነት" በሚል ርዕስ ላይ መልዕክቴን አስነብባቹዋለው። -----------ደህና ሁኑ ጌታ ይባርካችሁ።